# Learning by Ear 2013

**«መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ—«መዘዙን መቀበል»**

EPISODE 8: የሴቶች ወግ

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Daniel Pelz, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: ምህረት PUKES**

- **ብሩክ (M, 8)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**
- **ምህረት (F, 15)**

**SCENE 2: AT ትዕግስት'S**

- **ትዕግስት (F, 15)**
- **የትዕግስት እናት (F, LATE 30'S)**

**SCENE 3: ዳንኤል AND ዳንኤል PLAY BASKETBALL**

- **ዳንኤል (M, 16)**
- **በለጠ (M, 16)**

**SCENE 4: AT THE MSOTO FAMILY HOME IN TANDIKA**

- **ቅዱስ (M, 8)**
- **ብሩክ (M, 8)**

- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**
- **ምህረት (F, 15)**

**<u>INTRO</u>**

**1. NARRATOR:**

**ጤና ይስጥልን «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ—«መዘዙን መቀበል» የተሰኘው ድራማችን ተከታታዮች። በታዳጊዎቹ ምህረት፣ ትዕግስት፣ ንጉሴ እና ዳንኤል ህይወት ውስጥ በቅርቡ ብዙ ነገሮች ተከስተዋል። ትዕግስት በአድሜ እጅጉን ከሚበልጣት የቀድሞ ፍቅረኛዋ ምኖቴ የሚያስገርም ጥያቄ ቀርቦላት ነበር። አብረው መኖር እንዲጀምሩ መፈለጉን ነግሯታል። ባለፈው ክፍል ጭውውት ግን ምኖቴ ይህንን ለምን  እንደፈለገ  ተረድተናል። — እናቱ ናቸው ምክንያቱ!:**

**2. EPISODE 7, LINES 65 – 69 (alternative: starting from line 61):**

***MABEL:* *እሺ ምኖቴ። በል እስቲ ንገረኝ። መቼ ነው የምታገባውና የልጅ ልጆች የማየው? (…)***

***MANOTI:* *የሆነ ነገር በላሽ?***

***MABEL:* *የምልህን ትሰማለህ ምኖቴ? በል ፈጠን በልና የልጅ ልጅ አምጣልኝ።***

**3. NARRATOR:**

**የትዕግስት ሁነኛ ጓደኛ ምህረት አርግዛለች። እናም ፅንሱን እስድታስወርድ ለማሳመን አባትየው ዳንኤል የተቻለውን ያህል እየጣረ ነው:**

**4. EPISODE 7, LINES 29 – 30:**

*ዳንኤል:  ተመልሰን አብረን እንድንሆን እፈልጋለሁ። ግን ፅንሱን ማስወረድ አለብሽ ምህረት።*

*ምህረት: አሀ! እሄ ሁላ ለዚህ ነው እንዴ? (...)*

**5. NARRATOR:**

**የዛሬው ክፍል ጭውውት  « የሴቶች ወግ» ይሰኛል። ዘና ብላቹህ ተቀመጡ እና ከኛ ጋ በሀሳብ ወደ ታንዲካ የጎስቋሎች መንደር  ዝለቁ። እዛም ምህረት፣ እናቷ እና ሁለቱ ወንድሞቿ ይኖራሉ። እስኪ ቀናቸው እንዴት እንደሚጀምር እንስማ።**

**<u>SCENE 1: ምህረት PUKES</u>**

**6. ATMO: MORNING IN TANDIKA SLUMS, INTERIOR ATMO**

***KW BEGIN***

**7. ብሩክ:** **(coughs)**

**8. ወ/ሮ ሉሊት:** **ብሩክ ይኼ ሳልህ አልተሻለህም እንዴ? ለመሆኑ ሎሚ በውሃህን እየጠጣህ ነው?**

**9. ብሩክ:** **(coughs) አዎ እማ!**

**10. SFX: ምህረት BEING SHAKEN**

**11. ወ/ሮ ሉሊት:** **ምህረት ተነሽ እኮ ነው የምለው! እዚህ ፍራሽ ላይ ቀኑን ሙሉ ተኝተሽ ልትውይ ነው እንዴ? መቼም ይሄ ፍራሽ ብን አለማለቱምይደንቀኛል።**

**12. ምህረት:** **(grumbles sleepily and mumbles under blanket)**

**13. ወ/ሮ ሉሊት:** **ምንድን ነው ያልሽው? አልሰማሁሽም።**

***KW END***

**14.** ምህረት: **(lazily and moodily)** እማ ለምንድን ነው በጠዋት መነሳት ያለብኝ። ቅዳሜ እኮነው።

**15.** ወ/ሮ ሉሊት: እኔ ስላዘዝኩሽ። ተነሽና አሁን ከሰል ግዢልኝ። ፖሊስ ጣቢያ ከመሄዴ በፊት ይህንን ልብስ መተኮስ አለብኝ።

**16.** ምህረት: **(rudely)** ኸ ለምን ራስሽ ከሰሉን አትገዢም እኔ ደክሞኛል።

**17.** ወ/ሮ ሉሊት: **(stern)** ምን አልሽ?

**18.** ምህረት: ምንም.

**19.** ብሩክ: እማ አባዬን ለመጠየቅ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ልትሄጂ ነው? አሁንም እንደታሰረ ነው እንዴ?

**20.** ወ/ሮ ሉሊት: አዎ ብሩኬ። አባትህ አሁንም እዛው ነው። አሁን ግን እሱን ልጠይቅ አይደለም የምሄደው። ሌላ የማከናውናቸው አንዳንድ ነገሮች ስላሉኝ ነው።

**(to ምህረት)** ስሚኝ ወይዘሪት አልጎምጓሚት…

**21. SFX: BLANKET PULLED AWAY**

**22.** ወ/ሮ ሉሊት: ከዚህ ብርድ ልብስ ውስጥ አሁኑኑ ውጪ ። ምንድን ነው የሆንሽው አንቺ ልጅ?

**23. SFX:** ምህረት **STANDING UP**

**24.** ምህረት: **(to herself)** ወይ ጉድ….

**25. SFX: RUNNING FOOTSTEPS (BAREFOOT) LEAVE**

**26.** ወ/ሮ ሉሊት: አንቺን እኮ ነው… ምህረት የሌሊት ልብስሽን ለብሰሽ ወዴት ነው የምትሄጂው? ተመለሽ ዋ! ምህረት! ምህረት!

**(to herself)** ይህቺ ልጅ ምን ሆናለች?

**27.** ምህረት: **(PUKES OUTSIDE)**

**28. SFX: SOUND OF SOMEBODY PUKING OUTSIDE**

**29.** ወ/ሮ ሉሊት: **(Shouts)** ምህረት! አሞሻል እንዴ? ምህረት!

**30. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 2: AT ትዕግስት’S</u>**

**31. ATMO: RADIO MUSIC IN THE BACKGROUND**

**32. SFX:** ትዕግስት**’S CELLPHONE RINGS**

**33. SFX: BED CREAKS**

**34.** ትዕግስት: **(yawns; to herself)** ወይኔ! እናቴ ናት።

**35. SFX: BEEP AS CALL IS ANSWERED**

**36.** ትዕግስት: ታድያስ እማዬ

**37.** የትዕግስት እናት: **(on phone)** ታድያስ ትዕግስቴ የኔ ልጅ። እንደምን አለሽ? ትናንት ልትደውይልኝ ሞክረሽ ነበር?

**38.** ትዕግስት: አዎ! ለምንድን ነው ስልኩን ያላነሳሽው? የት ነው ያለሽው?

***KW BEGIN***

**39.** የትዕግስት እናት: **(ignores the question)** ምን ልትይኝ ፈልገሽ ነበር?

**40.** ትዕግስት: እማ መቼ ነው ወደ ቤት ተመልሰሽ የምትመጪው?

**41.** የትዕግስት እናት: በቅርቡ ትዕግስቴ። በጣም በቅርቡ።

**42.** ትዕግስት: ግን ከሄድሽ እኮ ከ ሳምንት በላይ ሆነሽ። እዚህ እንድትሆኚ አፈልጋለሁ። ሰራተኛዋን ከአባረርሻት ጀምሮ እቤት ውስጥ ብቻዬን ነኝ። … ምን እንደምበላም አላውቅም።…

**43.** የትዕግስት እናት: **(cuts in)** የገዛሁት ምግብ አለቀ እንዴ?

**44.** ትዕግስት: ማለት ይቻላል። እንዴ! ብዙ ምግብ ትተሽ አልሄድሽም እኮ።

**45.** የትዕግስት እናት: እስቲ እንደ ስምሽ ትዕግስት ይኑርሽ  አንቺ ልጅ። በይ አሁን የተወሰነ ገንዘብ እልክልሻለሁ እሺ?

**46.** ትዕግስት: **(desperate)** ግን እማዬ ለምንድን ነው ጨርሶ ከቤት የጠፋሽሽው?የት ነው ያለሽው?

***KW END***

**47.** የትዕግስት እናት: አሁን ትልቅ ልጅ ሆነሻል። ትዕግስት አዳምጪኝ --

**48.** ትዕግስት: ሁልጊዜ አዳምጪኝ እንዳልሽ ነው። ከአሁን በኋላ ምንም ነገር መስማት አልፈልግም።  አሁን አርፈሽ ወደቤት ነይ— ካለበለዚያ ከምኞቴ ጋ አብሬ መኖር እጀምራለሁ።  እንደውም እሱ አብረን እንድንኖር ጠይቆኛል።

**49.** የትዕግስት እናት: **(shocked)** ምን? ትዕግስት! ምኞቴ ደግሞ ማነው?

**50.** ትዕግስት: እሱ ማ--

**51.** የትዕግስት እናት: **(cuts her short, firm)** ወይዘሪት፤ አሁን እኔ የምልሽን አድምጪኝ። አደራ እንዲያ ያለ ነገር አንዲት እንዳታደርጊ። ለማግባት ገና ጊዜሽ አይደለም።

**52.** ትዕግስት: ላገባ እኮ አይደለም። ከሱ ጋ ብቻ አብሮ መኖር መጀመር ነው።

**53.** የትዕግስት እናት: ይኼ አነሰም በዛም ያው ነው።

**54.** ትዕግስት: ለማን እንደምትናገሪ አያስተዋልሽ። እንደውም አንቺ ነሽ ወንዶችን እንደ ሸሚዝ የምትቀያይሪያቸው። እኔ በአንድ ልፅና ነው ያልኩት።

**55.** የትዕግስት እናት: ከኔ ጋ ሁለተኛ እንደዚህ እንዳትነጋገሪ። እናትሽ እኮ ነኝ አንቺ!

**56.** ትዕግስት: እንደዛ ከሆነ ነይ ወደቤት!

**57.** የትዕግስት እናት: እሺ እመጣለሁ።

**58.** ትዕግስት: መቼ? አሁኑኑ እፈልግሻለሁ!

**59.** የትዕግስት እናት: በቅርቡ ትዕግስቴ። የምልሽን ብቻ ስሚ። አባትሽ ከኔ ጋ እንደማትኖሪ ከደረሰበት ትምህርት ቤት አትሄጂም የቤት ኪራያችንንም መክፈሉን ያቆማል።

**60.** ትዕግስት: **(crying)** አንቺን የሚያሳስብሽ ነገር ቢኖር የቤት ኪራይ ብቻ ነው አይደል። ምን እንደምበላ እንኳን ጉዳይሽ አይደለም። ታውቂያለሽ? እንደውም ወደ ቤት መመለሱ ያን ያህል አያሳስብሽ እሺ። ምናልባት ስትመለሺ ከምኖቴ ጋ ተጋብተን ይሆናል።

**61.** የትዕግስት እናት: **(pleading)** ትዕግስትዬ ! ቆይኝ እስኪ አንዴ! **(deep breath)** እሺ። ከዚህ ከምኞቴ ጋ መኖሩን ከልብ ከሆነ የምትፈልጊው በቃ እሺ ሂጂ ግቢ። ግን ትምህርት ቤት መሄድሽን እንደማታቋርጪ ቃል ግቢልኝ። እሺ? ካለበለዚያ--

**62.** ትዕግስት: **(cuts in, angry)** አው። ይገባኛል። የቤቱ ኪራይ …በቃ ተይኝ ከእንግዲህ ያንቺ ልጅ አይደለሁም።

**63. SFX: PHONE DISCONNECTS**

**64.** ትዕግስት: **(cries)**

**65. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: ዳንኤል AND በለጠ PLAY BASKETBALL</u>**

**66. BONGO ACADEMY: OUTSIDE, WEEKEND, DAYTIME**

**67. SFX: BASKETBALL BEING DRIBBLED**

**68.** በለጠ: **(Heavy panting)**ኧኸ! በልሺ ንገረኛ አሁን ወንዱ ማነው? ንገረኝ ። ወንዱ ማን ነው? ዳንኤል እኔንማ አልፈህ መሄድ አትችልም። ስማ « በርሚሉ በሌ» እያሉ ሲጠሩኝ እኮ ያለነገር አይደለም እሺ።

**69.** ዳንኤል: **(Pants as he dribbles)** በርሜሉ በሌ ለሚናገረው ቢጠነቀቅ ይሻለዋል። – ይሄውልሽ እዚጋ እንግዲህ «ዳኒ ኳስ አንደባላዩን" ተመልከቺያት!

**70. SFX: SCUFFLE AND DRIBBLING AS THEY PLAY BASKETBALL**

71. ዳንኤል: እንዲህ ትዞራለች። ሮጥ ሮጥ ትልናአንዴ ትዘላለች— ከዛም እንዲህ ነጥብታስቆጥራለች!

72. **SFX: BASKETBALL BEING THROWN INTO BASKET**

73. ዳንኤል: **(Laughs)** “በርሚሉ በለጠ አያስቆመኝም።!

74. በለጠ: **(Still panting)** አረ ዳኒ አታካብጂ!

75. ዳንኤል: **(Laughs)** እንደውም ከእዚህ የበለጠ ትፈልጋለህ?

76. በለጠ: አይ። እረፍት ነው የምፈልገው። እንቀመጥ።

77. ዳንኤል: እሺ

78. **SFX: RUSTLING OF CLOTHES AS THEY SIT**

79. በለጠ: **(Catches his breath)** እረ ዳንኤል –ከምህረት ጋ ግን እንዴት አለፈ? በአሪፉ አናገርካት?

80. ዳንኤል: አዎ። ልክ አንተ እንዳልከኝ።

81. በለጠ: እናስ?

82. ዳንኤል: የሰራ አልመሰለኝም! በዛ ላይ መምህርት ሰብለ ለትንሽ ልትሰማን ነበር።

83. በለጠ: **(dismissive)** አይዞህ! ምህረት ይሄኔ እስካሁን አስወርዳዋለች። ስማ! “በርሚሉ በሌ» ምናልባት ቅርጫት ኳስ መጫወት በደንብ ጎበዝ ላይሆን ይችላል። ግን ምክር በመስጠት የሚያኽለው የለም።!

84. ዳንኤል: **(sarcastic)** ልክ ነህ። ወደፊት ፕሬዚዳንት ስሆን አማካሪዬ አድርጌ እንድቀጥርህ አስታውሰኝ።

***KW BEGIN***

**85.** በለጠ: **(laughs)** የተገላቢጦሽ ነው ወዳጄ!

**86.** ዳንኤል: ከምሬ ነው የምልህ። ለድጋፍህ አመሰግናለሁ በለጠ።

**87.** በለጠ: ምንም አይደል። እኔ ላንተ ለምን ከባቡር ፊት ለፊት አይሆንም እቆምልሀለሁ --

**88.** ዳንኤል: **(cuts in)** አዎ ይገባኛል። --

**89.** በለጠ: --እስካልተንቀሳጠሰ ድረስ ማለቴ ነው! **(Laughs)**

**90.** ዳንኤል: አንተ ደደብ! **(they laugh)**

***KW END***

**91. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 4: AT THE MSOTO FAMILY HOME IN TANDIKA**

**92. SFX: INTERIOR ATMO, TANDIKA SLUMS, MORNING**

**93.** ብሩክ/ቅዱስ: **EATING**

**94. SFX: SPOONING PORRIDGE**

**95.** ብሩክ: እማ ምህረትን አሟታል እንዴ?

**96.** ወ/ሮ ሉሊት: እኔ አላውቅም።ብሩኬ

**97.** ብሩክ: ስታስታውክ ነበር። ሰዎች የሚያስታውኩት ሲያማቸው አይደል እንዴ? **(coughs)**

**98.** ወ/ሮ ሉሊት: ቅንጩያችሁን ብሉና ጨርሱ ልጆች። ብሩክ ውሃ በሎሚ መጠጣትህን እንዳትረሳ።

**99.** ብሩክ: **(drinks)**

**100.** ቅዱስ: **(eats)**

**101. SFX: DOOR OPENS, FOOTSTEPS (BAREFOOT) APPROACH**

**102.** ወ/ሮ ሉሊት: ስለእሷ ስናወራ እቻት መጣች። ምህረት ነይ ተቀመጭ።

**103. SFX: RUSTLING OF CLOTHES**

**104.** ወ/ሮ ሉሊት: ልጆች ሂዱ ውጡና ተጫወቱ። ምህረት ነይ ላናግርሽ እፈልጋለሁ።

**105.** ቅዱስ: **(mouth full)** እማ ገና በልተን አልጨረስንም እኮ --

**106.** ወ/ሮ ሉሊት: **(stern)** በኋላ ትጨርሳላችሁ። ሂዱ ውጡ አሁን።

**107.** ቅዱስ/ብሩክ: እሺ…

**108. SFX: FOOTSTEPS (2 KIDS), DOOR OPENS, SHUTS.**

**109.** ወ/ሮ ሉሊት: በይ ምህረት አሁን ብቻችንን ነን።

**(deep breath, struggles to get the words out)** I …

ለመሆኑ … **(deep breath)** ምህረት ዕርጉዝ ነሽ እንዴ?

**110.** ምህረት: **(caught)** እማ!

**111.** ወ/ሮ ሉሊት: ንገሪኝ ብያለሁ። አሁን ሶስተኛ ቀንሽ ነው ጠዋት ላይ ሲያስመልስሽ።

ምልዕክቶቹን አውቃለሁ።

***KW BEGIN***

**112.** ምህረት: ምንም አልሆንኩ እማ! ትንሽ ሳያመኝ አልቀረም። ለዛ ነው።

**113.** ወ/ሮ ሉሊት: ምህረት። ቂል አረግሽኝ እንዴ? ለኔ ካልነገርሽ ለማን ልትነግሪ ነው

ታዲያ? ቃል እገባልሻለሁ አልቆጣም።

**114.** ምህረት: **(cries)** እኔ… እማ…በጣም ይቅርታ!

**115.** ወ/ሮ ሉሊት: **(angry)** የሰማዕቱ ያለህ! ምንድን ነው የሆንሽው? ይህን ነው አሁን አሁን ትምህርት ቤት የሚያስተምሯችሁ። አይምሮ የለሽም?

***KW END***

**116.** ምህረት: **(cries more)** ይቅርታ እማዬ ይህ እንዲከሰት ፈልጌ አልነበረም…

**117.** ወ/ሮ ሉሊት: በይ እሺ አሁን ማን ነው ልጁ?

**118.** ምህረት: **(cries)**

**119.** ወ/ሮ ሉሊት: መልሽልኝ። ማን ነው?

**120.** ምህረት: ዳንኤል ይባላል። ከላቦሪያ ነው። የመጣው። …

**121.** ወ/ሮ ሉሊት: እ…ያውም የውጭ ሀገር ዜጋ። ጭራሽ ካልጠፋ ሰው ለማርገዝ የውጭ ሀገር ሰው መረጥሽ! ውጪ! ከአይኔ ከእይታዬ ጥፊልኝ አሁኑኑ!

**122.** ምህረት: **(cries)**

**123. SFX: RUNNING FOOTSTEPS (**ምህረት**)**

**124. SFX: DOOR OPENS AND CLOSES**

**125.** ወ/ሮ ሉሊት: ውይ ውይ ውይ ! ምን ጉድ ነው። ይህንን እኔ አላምንም። ከአቅሜ በላይ ነው።

## 126. OUTRO – NARRATOR:

**የምህረት እናት ወ/ሮ ሉሊት አልቆጣም ቢሉም ቃላቸውን አልጠበቁም።ምህረት አሁን ምን ታደርግ ይሆን? ፖሊስ ጣቢያ  ስስካሁን ታስረው ያሉት የምህረት አባትስ?  ይህንን ለማወቅ «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ»  የተሰኘውን ተከታታዩን የበማድመጥ መማር ሬዲዮ ድራማችን ተከታተሉ።  ከዚህ በፊት የተላለፉት ጭውውቶች አምልጥዎ ከነበር ሁሉንም** dw.de/lbe **ድረ ገፅ ላይ ያገኟቸዋል።** dw.de/amharic **የዶይቸ ቬለ የአማርኛው ድረገፅ ነው። ደህና ሁኑ**!